በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፕላንና ልማት ኮሚሽን

# የ2014 በጀት አመት ዕቅድ

ሀምሌ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

መግቢያ .................................................................................................................................1

ክፍል 1፡- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች ......................................................................................2

1.1 የኮሚሽኑ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶች፣ ዓላማ ________________________________________________2

1.2. የኮሚሽኑ የ2014-2017 በጀት ዓመት ተቋማዊ ስትራቴጅክ ዕቅድ ___________________________________3

1.3 የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም አጭር ግምገማ _______________________________________________3

1.4 በ2014 በጀት ዓመት ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ተግባራት ____________________________________6

ክፍል 2: - የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ........................................................................................................7

2.1. የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች (ክብደት 5) ____________________________________________________7

2.2. የኮሚሽኑ ዋና ዋና ግቦች የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ____________________________________________8

ሠንጠረዥ 1፡- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት፣ የዕቅድ መለኪያዎች እና የድርጊት መርሃ-ግብር _____23

ሠንጠረዥ 2፡- ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ በጀት ........................................................................55

መልካም አጋጣሚዎች .................................................................................................................55

ስጋቶች .......................................................................................................................................56

የመፍትሔ ሃሳቦች .........................................................................................................................56

## መግቢያ

የፕላንና ልማት ኮሚሽን ተልዕኮ ኢኮኖሚውን በረጅምና በመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ በመምራት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲሁም ዘላቂና ፍትሀዊ ልማት እንዲረጋገጥ ማስቻል ሲሆን ዓላማውም በተመጣጠነ ሀገር አቀፍ የዕድገት ማዕቀፍና የአስር ዓመታት የረጅም ዘመን መሪ የልማት ፕላን ላይ በመመስረት የአምስት ዓመት ሀገራዊ የልማት ፕላን ማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን በየጊዜው መከታተልና መገምገም ነው።

ከዚህ አንፃር በ2014 በጀት ዓመት በርካታ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ተግባራትን ለማከናወን ያቀደ ሲሆን ከነዚህም መካከል የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ማስተግበሪያ ስልቶች ተጨማሪ ሰነድ ማዘጋጀት፣ የ30 ዓመት የልማት ዕቅድ ዝግጅትን ማጠናቀቅ፣ የአንድ ዓመት እና የሶስት ዓመት የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀም ሪፖርቶች ማዘጋጀት፣ ሀገራዊ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓትን በማጠናከርና የልማት ዕቅድ ትግበራ አፈጻጸምን በመተከታተልና የክትትልና ግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ውጤቱንም ለሕዘብ ይፋ በማድረግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ የልማት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትልና ግምገማ ለማካሄድ የሚያግዙ ሀገራዊ አድማስ ያላቸው ጥናቶችን ማካሄድ.፣ የብሔራዊ አካውንት መረጃዎችን ማመንጨት፣ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ ማካሄድ እና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን አቅዷል። ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ያቀዳቸውን ዋና ዋና ሀገራዊ ስራዎች ለመፈፀምና በብቃት ለመወጣት ተቋማዊ አደረጃጀቱንና የሰው ኃይሉን ለማጠናከር አቅዷል።

የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በዋናነት የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም በመገምገም ሳይጠናቀቁ ወደ በጀት ዓመቱ የተዘዋወሩ እና የተቋሙ ስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ በግብ የተቀመጡ ተግባራትንና ውጤቶችን ለማሳካት ያለመ ነው። የዕቅዱ መነሻዎችም የኮሚሽኑ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንዲሁም የተቋሙ ስትራቴጅክ ዕቅድ ናቸው። የዕቅዱ ይዘት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን ክፍል አንድ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ነው። ክፍል ሁለት በ2014 በጀት ዓመት የታቀዱ ተግባራትን፣ የዕቅድ መለኪያዎች እና የድርጊት መርሃ-ግብር አካቷል።

## ክፍል 1፡- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች

የ2014 በጀት አመት ዕቅድን ለማዘጋጀት መነሻ የተደረጉት የኮሚሽኑ ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ የተሰጡት ተግባርና ሃላፊነቶች እንዲሁም የ2014-2017 በጀት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ናቸው፡፡

### 1.1 የኮሚሽኑ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶች፣ ዓላማ

### ሀ) የኮሚሽኑ ተልዕኮ

- ለአገሪቱ ዘርፈ ብዙ የልማት መስኮች የፖሊሲ ትንታኔዎችን፣ አመራር እና ድጋፍ መስጠት
- የሴክተር መስሪያ ቤቶችን እና የመንግሥት ተቋማትን በማቀናጀት የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት እቅዶችን ማዘጋጀት
- ለልማት ፖሊሲ፣ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች መረጣ፣ ግምገማ እንዲሁም ቅደም ተከተል እንዲረዳ የመንግሥት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና አመራር አቅም ማጎልበቻዎችን ማበልፀግ
- በልማት እቅዶች፣ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች ላይ ወቅቱን ጠብቆ ቁጥጥር እና ግምገማ ማካሄድ
- ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት እና ሌሎች የማክሮ ኢኮኖሚ ግመታዎችን ከሴክተሮች ትንታኔ ጋር ያጠቃለለ መደበኛ አካውንት ማዘጋጀት

### ለ) የኮሚሽኑ ራዕይ

ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት ማድረግ

### ሐ) የኮሚሽኑ እሴቶች

- ተግባቦትን መፍጠር/Communication
- ሙያን ማክበር/Professionalism
- ታማኝነት/Integrity
- ትጋት/Drive
- ፈጠሪነት/Innovation
- ልህቀት/Excellence

### መ) የኮሚሽኑ ዓላማ

የኮሚሽኑ አላማ ሁሉም አገራዊ የልማት እቅዶች በአግባቡ የታለመላቸውን ግብ መምታቸውን ማረጋገጥ

### 1.2. የኮሚሽኑ የ2014-2017 በጀት ዓመት ተቋማዊ ስትራቴጅክ ዕቅድ

ለ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ዋናው መነሻ ኮሚሽኑ በሚኖረው አዲስ አደረጃጀት ከተግባርና ሀላፊነቱ የተመነዘረ ከ2014-2017 በጀት ዓመት የሚቆይ ስትራቴጅክ ዕቅድ ሲሆን በዚህ ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ እና በ2014 በጀት ዓመት ሊሰሩ የታቀዱትን ግቦችና ተግባራት በመውሰድና በማዳበር በዚህ እቅድ እንዲካተቱ ተደርጓል።

### 1.3 የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም አጭር ግምገማ

- የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ተጠናቆ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል። የልማት ዕቅዱ አጭር ሰነድ ተዘጋጅቷል። የልማት ዕቅዱን ወደ እንግሊዘኛ የመተርጎም ስራ ተሰርቶ ሁለተኛ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል። ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሰነዱን በሶፍት ኮፒ በመስጠትና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት ክልሎችና የከተማ አሰትዳደሮች ዕቅዶቻቸውን ከሀገራዊ ዕቅዱ ጋር እንዲያጣጥሙ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። የ10 ዓመቱ ዕቅድ ማስፈጸሚያ የሚሆን የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂ/ዕቅድ ለማዘጋጀት የሰው ሃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን (skill mismatch) ለማስወገድና ከኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አቅርቦትን ለማረጋገጥ ከስራ ፈጠራ ኮሚሽን ጋር በመሆን በተመረጡ 11 ዋና ዋና ዘርፎች ላይ መነሻ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል።

- ኢትዮጵያ በ2050 ከአፍሪካ ሁለት ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገራት አንዷ ለማድረግ፣ ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ፣ የማኑፋክቸሪንግ ማዕከል ለማድረግ፣ ለሁሉም ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የሚችል ኢኮኖሚ ለመገንባትና ድህነትን በሁሉም መገለጫ ለማጥፋ የሚያስችላት የ30 ዓመት ዕቅድ ዕቅድ በመዘጋጀት ላይ ነው። በዚህም የተቀናጀ የፕላኒንግ ሞዴል የተዘጋጀ ሲሆን የፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ መነሻ ሀሳቦች (Envisioned Policy Directions) ተለይተዋል፡ ፡ በተመረጡት የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሀገራት (ማሌዥያ፣ ኮሪያ፣ ቬትናም፣ ታይላንድ፣ ፊሊፒንስ፣ ኢንዶኔዥያ) ምጣኔ ሀብታቸው ምን እንደሚመስል ሪቨው የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

- ከሀገራዊ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ የተመነዘረ እና ከዘላቂ የልማት ግቦች፣ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም በዘርፎች መካከል በምርት ግብዓት፣ በቴክኖሎጂና በሰው ሀይል ፍላጎቶች የተሳሰረ ዝርዝር ሀገራዊ የመከከለኛ ዘመን ዕቅድ (2013-2017) ተዘጋጅቷል።

- የ2012 በጀት ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም የሚያሳይ ሪፖርት እንዲሁም የ2013 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው ተቋማት እንዲደርሱ ተደርጓል። የ2013 በጀት ዓመት የስድስት ወር የEconomy digest ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

- የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የአምስት ዓመት የዕቅድ ማጠቃለያ የግምገማ ሪፖርት በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቅጂዎች ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የቅድመ-ዝግጅት ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን የግምገማ ተግባሩን ለማከናወን የሚያስችል የሥራ መዘርዝር፣ የበጀት ግምት እና የሥራ ማስታወቂያ በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም በኩል እንዲወጣ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

- በተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የመስክ ዳሰሳና ጥናት ለማካሄድ መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ፕሮጀክቶች በአፈፃፀም ደረጃቸው ተለይተው ከሌሎች ተቋማር ጋር በመቀናጀት በ15 የመስኖና የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ጉብኝት ተካሂዷል።

- ቁልፍ የውጤት አመልካቾቹ ለአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ፖሊሲ ማትሪክስ ዝግጅት ግብዓት/መነሻ እንዲውል ለዘርፍ አስፈጻሚ መ/ቤቶች እንዲደርሳቸው ከመደረጉም በላይ የክለሳ ስራው ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል።

- ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የታገዘ የክትትልና የሪፖርት አሰራር ስርዓቱ (Digital Monitoring and Reporting System) ይፋ ተደርጓል። አስፈላጊው ዝግጅት በማድረግ (ስትሪንግና ቴክኒካል ኮሚቴ በማዋቀር፣ አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟላትና የመረጃ መረብ ኦዲት ሥራ በማከናወን) የክትትልና ግምገማ ማከናወኛ ሶፍትዌር ተዘጋጅቶ የሙከራ ሥራው እየተከናወነ ይገኛል።

- የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ወጥ በማድረግ የስራ ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲሁም የሁሉንም አካላት ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት (Master Reporting) እንዲኖር የሚያስችል የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ (Checklist) ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት በሕዝብ ተወካዮች በኩል ተደራሽ ተደርጓል።

- በዘርፈ ብዙ የድህነት አመላካች ምንነት ላይ መሰረታዊ የፅንሰ ሃሳብ ይዘት ላይ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ስልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም በሰነዱ ዝግጅት ላይ ለሚሳተፉ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት መሰረታዊ የስታታ ሶፍት ዌር፣ የሰርቨይ መረጃ አጠቃቀም እና ከድህነት ትንተና ጋር የተያያዘ ዝርዝር ስልጠና ተሰጥቷል።

- በዋጋ ግሽበት መንስዔዎች ዙሪያ Fundamental Sources of Inflation በሚል የተጀመረውን ጥናት በተመለከተ መረጃዎችንና የተዘማች ጽሑፎች ዳሰሳ መሠረት በማድረግ ረቂቅ ሪፖርት የማዘጋጀትና አስተያየት የመሰብሰብ ስራዎች ተሰርቶ የመጨረሻው ሪፖርት በማዘጋጀት ለማክሮ ኮሚቴ ቀርቧል።

- ሀገራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ የሚያስችል ዝርዝር የድርጊት መረሀ ግብር ተዘጋጅቶ በፖሊሲ ጥናት ኢንሲቱይት በኩል ጥናቱ እየተከናወነ ይገኛል።

- ሲስተምስ ዳይናሚክስ ሞዴል (Systems Dynamics Model) ቀረፃ ሥራ ግብዓት የሚሆኑ ቀሪ መረጃዎችን በመሰብሰብና ወደ ሞዴሉ በማካተት በረቂቅ ደረጃ ሥራው ለማጠናቀቅ ተችሏል። ለኮሚሽኑ እንዲሁም ለአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ለሚገኙ ባለሙያዎች በኢኮኖሚ ሞዴሎች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል። Social Account Matrix (SAM) በረቂቅ ደረጃ ሥራው ለማጠናቀቅ ተችሏል።

- 197 የፕሮጀክቶች ፅንሰ ሀሳብ ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ቀርበው 121 ፕሮጀክቶች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ምልመላ በማከናወን እና ፕሮጀክቶቹን ካቀረቡት መስሪያ ቤቶች ላይ ምክክር በማድረግ ተቀባይነት ያገኙ፣ ተጨማሪ ማሻሻያ የሚጠይቁ እና ተቀባይነት ያላገኙ በሚል ተመድበው ለአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ምላሽ ተሰጥቷል። 61 ፕሮጀክቶች ወደ ቀጣይ ሂደት ማለትም ወደ ዝርዝር አዋጭነት ጥናት እንዲሸጋሩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

- መቀናጀት (Integrate) ያለባቸው ፕሮጀክቶች እንዲቀናጁ እንዲሁም አስፈፃሚ መ/ቤቶች ወደ ቀጣይ ሂደት ያለፉ ፕሮጀክቶችን ለማጥናት እየሰሩ ያሉትን ስራዎች ላይ በታቀደው መልክ ክትትል ተካሂዷል፤ አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ ድጋፎች ተሰጥተዋል።

- ከ17 አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ለተውጣጡ 50 ሰልጣኞች በአምስት ሴክተሮች የአዋጭነት ግምገማ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል። ለጤና ሚኒስቴር፣ ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ለውሃ ኮሚሽን እና ለተፋሰስ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች በፌደራል መንግስት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር አዋጅ እና አዋጁን መሰረት አድርገው በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናውነዋል።

- ባለፉት 10 አመታት የመንግስት ኢንቨስትመንት ትንተና መነሻ ተዘጋጅቷል፣ ለመንግስት ኢንቨስትመንት ፕላን ዝግጅት የሚሆኑ መረጃዎችን የማሳባሰብ ሂደት ተጀምሯል፡፡

- የ2012 በ.ዓ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ከአቅርቦት አንፃር (Supply Side GDP) ግምት እና ጥቅም ላይ ከዋለበት አንፃር (Expenditure Side GDP) ተዘጋጅቷል፡፡

- የ2013 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት የብሄራዊ አካውንት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በ (Supply Side GDP) ግምት ተዘጋጅቷል፡፡

- የ2008 መረጃ በመጠቀም የምርት አቅርቦትና አጠቃቀም ሚዛን ሠንጠረዥ (Supply and Use Table (SUT)) ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

- የክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃዎች ከብሔራዊ አካውንት አሠራር ጋር በተጣጣመና በተቀናጀ መልኩ ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ከሀረሪ፣ ለደቡብ እና ለሲዳማ ክልል ጋር ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት የማጎልበት ስራ እና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል።

- ከዘጠኝ ክልሎችና ከሁለት ከተማ መስተዳደሮች ለተውጣጡ 22 ባለሙያዎች በብሔራዊ/ክልላዊ ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች እና የቋሚ አመት ለውጥ ዙሪያ ላይ የተግባር (Practical) ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አፈጻጸም ግምገማ ጥናት ውጤት ለባለደርሻ አካላት ተሰራጭቷል፡፡ የፖሊሲውን ክለሳ ለማካሄድ ቢጋር /TOR/ ተዘጋጅቶ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት በቢጋሩ ላይ አስተያየት ተሰቶበታል፡፡

- ከኢትዮጵያ ሳይንስ አካደሚ ጋር በመተባበር ‘’What is the nexus among Ethiopia's fertility rate, unemployment and migration and assessing the management of the nexus” በሚል ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ የቅድመ ጥናት ውይይት የተደረገ ሲሆን በቀጣይ ጥናቱ በጋራ የሚከናወንበትን መንገድ በማመቻቸት የሚካሄድ ይሆናል፡፡

- የፖሊሲ መግለጫ/መመሪያ ለማጠናቀር “Pathways to Accelerate the Process of Demographic Dividend in Ethiopia” ፣ “Redressing Regional Disparities in Fertility Levels in Ethiopia: Priority Intervention Areas”, እና “Raising Age at First Marriage as a Factor Contributing to the Reduction of Fertility in Ethiopia” በተሰኙ ዋና ዋና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ቢጋር ተዘጋጅቶ የሪፖርቱ ጥንቅር ተጠናቋል፡፡

- በኢትዮጵያ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የውልደት ምጣኔ ያላቸው ክልሎች ውስጥ የስነ ህዝብ ትርፍ ድርሻ ተጠቃሚነት /harnessing demographic dividend/ ላይ ወቅታዊ ሁኔታውን ለመቃኘት የንፅፅር ጥናት ለማካሄድ የጥናቱን ቢጋር /TOR/ ተዘጋጅቷል፡፡

- ከ ICPD የናይሮቢ የጋራ ስምምነቶች /ግዴታዎች/ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁልፍ የሥነ-ህዝብ እና ልማት ጉዳዮች ላይ ስኬቶችን እና ክፍተቶችን የሚያሳይ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ

- የልማት ፕሮጀክቶችን አስተዳደር ሂደት (Project Cycle Management) ዲጂታል ለማድረግ ከገንዘብ ሚኒስቴር በቀረበ ፕሮፖዛል ላይ አስተያየት ተሠጥቷል፡፡

- በኢስንታቡል የድርጊት መርሃ-ግብር (IPOA) ላይ በተዘጋጀ የምክክር መድረክ አገራችን በተቋሙ ከፍተኛ ሃላፊዎች እንድትወከል በማድረግ ንግግር እንዲዘጋጅና የሀገሪቱ ፍላጎት እንዲቀርብና እንዲንፀባረቅ ተደርጓል።
- ከIGAD Disaster and Sustainabiltiy Initiative ጋር በመተባበር የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ተችሏል።
- በሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራርብ መመሪያ እና በአጠቃላይ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ ዙሪያ ከተቋማትና ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር ውይይትና ምክክሮች ተደርገው መግባባት ላይ ተደርሷል።
- በዕቅድ ክትትልና ግምገማ፣ በሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ዙሪያ በአጠቃላይ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ በተደረጉ የአሰራር ለውጦች ላይ ለክልሎች እና በርካታ የፌዴራል ተቋማት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።
- በኢትዮጵያ ኢቫልዮሽን ማህበር (Ethiopian Evalaution Association) ዓመታዊ ስብሰባ ላይ በመገኘት በአጠቃላይ ስለ 10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም በግምገማ አቅም ግንባታ ዙሪያ ስለሚሰሩ ስራዎች ገለፃ ተደርጓል። በተጨማሪም ማህበሩ በቀጣይ ከኮሚሽኑ ጋር ስለሚኖሩት የስራ ግንኙነቶች ውይይት ተደርጓል።
- በወጣቶች ፍልሰት ምክንያቶች፣ ተግዳሮቶችና መወሰድ ስለሚገባቸው የመፍትሄ ሃሰቦች ላይ ጥናት ለማድረግ የጥናቱ ቢጋር /TOR/ ተዘጋጅቶ ጥናቱን የሚያካሂድ ባለሙያ ኮሚሽኑ ባቋቋመው ኮሚቴ ተመርጦ የጥናቱ ስራ ተካሂዷል። የጥናቱ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ላይ አስተያየት ተሰቶበታል።

### 1.4 በ2014 በጀት ዓመት ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ተግባራት

ኮሚሽኑ የ2013 በጀት ዓመትን አፈፃፀም በመገምገም በበጀት ዓመቱ ታቅደው ያልተጠናቀቁ ተግባራትን ለማጠናቀቅ እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት ትኩረት የሚሰጣቸውን አዳዲስ ተግባራትን ለይቷል። በዚሁ መሠረት በ2014 በጀት ዓመት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የተጣጣመ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ
- የልማት ዕቅድና የልማት ፕሮጀክቶች ትግበራ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ
- የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ
- የልማት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትልና ግምገማ ከጥናትና ምርምር ጋር ያለውን ትስስር ማሳደግ
- የብሔራዊ ኢኮኖሚ አመላካች መረጃዎችን ማመንጨትን
- የልማት ፕሮጀክቶች ቅድመ-ትግበራ ግምገማ
- የስነ-ህዝብና ልማት ትስስር
- የድጋፍ ስራዎች

# ክፍል 2: - የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

## 2.1. የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች (ክብደት 5)

**የእቅድ ዝግጅት**

የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴት እና የ2013 በጀት አመት አፈጻጸም ግምገማ መነሻ ያደረገ የኮሚሽኑ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አሳታፊ በሆነ መልኩ ይዘጋጃል፡፡ የተዘጋጀው እቅድ በየደረጃው በመገምገም የማዳበር ስራ ከተሰራ በኋላ በበላይ አመራሩ ፀድቶ ለሚመለከታቸው አካላት ይላካል፡፡

ኮሚሽኑ ባለው አዲስ አደረጃጀት መሰረት ከተግባርና ሃላፊነቱ የተመነዘረ ከ2014-2017 በጀት ዓመት የሚቆይ ስትራቴጀክ ዕቅድ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

**የፈጻሚ ዝግጅት**

የኮሚሽኑን የሰው ሃብት 62 አዲስ ሠራተኞችን በመቅጠር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 250 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በ2014 በጀት አመት ዘመናዊ የሰው ሀብት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሲስተምን (ICSMIS) ወደ ሲስተሙ ያልገቡ ቀሪ የሰው ሃይል መረጃዎችን በማጠናቀር ተግባራዊ ማድረግ ታቅዷል፡፡

የአመራር እና ባለሙያ አቅም በረጅም፣በመካከለኛ እና በአጭር ጊዜ ትምህርትና ስልጠና መገንባትን በተመለከተ ለ6 የኮሚሽኑን ባለሙያዎች (የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ) የ2ኛ ዲግሪ (MA, MSc) እና የ3ኛ ዲግሪ (PhD) የትምህርት ዕድል ለማመቻቸት፣ ከሥራ ክፍሎች የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት፣ ለአዲስ ቅጥር ሰራተኞች ቅድመ ሥራ ማስተዋወቂያ (Induction) ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ስልጠና ለመስጠት እንዲሁም ለኮሚሽኑ ወጣት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለማመቻቸት ታቅዷል፡
:

ከዚህም በተጨማሪ የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ የድልድል የስንብትና ሌሎች ልዩ ልዩ የሰው ሀብት አስተዳደር መረጃዎችን የማጠናቀር ስራ ይሰራል፡፡

**የግብዓት ዝግጅት**

የኮሚሽኑን የ2013 አመታዊ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እና የ2014 በጀት ዓመት የስራ መርሃ-ግብር፣ የ2014 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄ በማዘጋጀት ለገንዘብ ሚኒስቴር ይላካሉ፡፡

የኮሚሽኑን የስራ ክፍሎች የግዢ ፍላጎት በማሰባሰብ በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት የተቋሙን የግዢ ዕቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲፀድቅ በማድረግ ግዢ የሚፈጸም ሲሆን የግዢ አፈፃፀም ሪፖርቶች ለሚመለከተው አካል ይላካሉ፡፡

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1.የተዘጋጀና የፀደቀ አመታዊ እና ስትራቴጂክ ዕቅድ

2.የተሟላ አቅሙ የተገነባ የሰው ሃብት

3.የተዘጋጀ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እና የስራ መርሃ-ግብር

4.የተዘጋጀ የግዢ ዕቅድ እና የግዢ አፈፃፀም ሪፖርት

## 2.2. የኮሚሽኑ ዋና ዋና ግቦች የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

## ስትራቴጂክ ግብ 1፡- የአሰራር እና የአገልግሎት አሠጣጥ ስርዓትን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)

ዋና ዋና ተግባራት

**ተግባር 1፡ የኮሚሽኑን የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ማጎልበት**

በኮሚሽኑ የዕቅድ አፈፃፀም ላይ በማኔጅመንት ስብሰባ በመወያየት የበላይ አመራሩ አቅጣጫዎችን ያመላክታል ለችግሮችም መፍትሔዎች ይሰጣል፡፡ የ2014 በጀት ዓመት የኮሚሽኑን የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች በመገምገም በወቅቱ ተዘጋጅተው ለተወካዮች ም/ቤት እና ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ይላካሉ፡፡

**ተግባር 2፡ ለኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች እና ለተጠሪ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ**

ከተጠሪ ተቋማት እና ከኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች በሩብ አመት አንድ ጊዜ/በየወሩ የስራ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት መርሃ ግብር ቀርጾ በወጣው መርሃ-ግብር መሰረት መደበኛ የስራ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

**ተግባር 3፡ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራዎችን መከታተል**

የኮሚሽኑን አመራርና ሰራተኞች ሃብትና ንብረት የማስመዝገብ፣ ተቋሟዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ የማዘጋጀት እና በተዘጋጀው ተቋሟዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ላይ ለተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ስልጠና የመስጠት፣ የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ተግባዊነትን የመከታተል፣ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን በመለየት ጥናት የማካሄድ እና በጥናት የተለዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመቅረፍ የሚሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

**ተግባር 4፡ የመንግሥት የፋይናንስ አሰራር ሥርዓትን በመከተል የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓትን ማጎልበት**

በ2014 በጀት ዓመት የፋይናንስ ሥርዓት በማጠናከር የመንግስት የፋይናንስ መመሪያዎችን የተከተሉ በጥሬ ገንዘብ ዕቅድ ላይ የተመሠረቱ ክፍያዎች ይፈፀማሉ፡፡ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠትና የውስጥ ቁጥጥርና ክትትልን ለማጠናከርም የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር ኢንፎርሜሽን (IFMIS) ሥርዓትን በመተግበር የኮሚሽኑን የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በየወቅቱ በማዘጋጀት ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለሚመለከታቸው አካላት ይላካሉ፡፡

**ተግባር 5፡ የውስጥ ኦዲት ሥራዎችን ማከናወን**

የኮሚሽኑ ሃብትና ንብረት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት የመዝጊያ ቆጠራ የማከናወንና የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የ2014 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የፋይናንስና የንብረት ኦዲት የማድረግ፣ የድንገተኛ ኦዲት፣

የክዋኔ ኦዲት እና የፕሮጀክት ሂሳቦችን እንደአስፈላጊነቱ የኦዲት ምርመራ የማከናወን እና በኦዲት ግኝቶች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ክትትል የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

**ተግባር 6፡ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

ለተቋሙ ሰራተኞች በህፃናትና በሴቶች መብት ዙሪያ፣ ፆታዊ ጥቃትና ኤች አይ ቪ ኤድስ ላይ እንዲሁም ለሴት ሰራተኞች በራስ የመተማመንና የአመራር ብቃትና ክህሎት ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና ለመስጠት፣ የህፃናት ማቆያ ግንባታን ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን የመከታተል እና በቅጥር፣ በደረጃ እድገትና በትምህርትና ስልጠና ምልመላ ላይ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ (Affermative action) ተግባራዊ መደረጉን የመከታተል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

**ተግባር 7፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና የዕውቀት ማኔጅመንት ሥራዎችን ማጎልበት**

በኮሚሽኑ አዲስ አደረጃጀት መሰረት የኢ-ሰርቪስ አገልግሎትን ለማስጀመር ድጋፍ የማድረግ፣ የገመድ አልባ ኢንተርኔት (WiFi) አገልግሎት የመስጠት፣ የኮሚሽኑ የኤሌክትሮኒክ ሜይል ሲስተምን እና ድረ-ገፅ የማስተዳደር፣ የተቋሙን ስብሰባዎች ቨርቹዋል የማድረግ፣ የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ስርዓት ትግበራን የማጠናከር፣ የመፃህፍት ግዢ የማከናወን፣ የቤተመፅሀፍት አገልግሎት የመስጠት (የንባብ አገልግሎት መስጠት፣ ማዋስ፣ ማስመለስ ወ.ዘ.ተ) ፣ እና ሌሎች ወቅታዊና ተጨማሪ ሥራዎችን (D-MRS ትግበራን ማጠናከር) ለማከናወን ታቅዷል፡፡

**ተግባር 8: - የህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ስራዎችን ማሳደግ**

**8.1፡ የኮሚሽኑን ተልእኮ ለማሳደግ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በመቀመር እንደ ታዳሚው ባህሪ አዋጭ በሆነው የመገናኛ ስልት የተመረጡ መልእክቶችን ማደራጀትና ማሰራጨት**

መረጃዎችን በማሰባሰብና በመቀመር ዜናና አርቲክል ለማዘጋጀት፣ በማህበራዊ ድረ-ገፅ አማካኝነት መረጃ ለማሰራጨት፣ የማህበራዊ ድረ-ገፅ ተከታዮቻችንን ለመጨመር እንዲሁም ህትመትና መገናኛ ብዙሃን በመጠቀም ወቅታዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ታቅዷል፡፡

**8.2፡ የውይይት መድረኮች በመምራትና በማስተባበር ውጤታማ የግብረ መልስ ስርአት በመዘርጋት ክህሎትንና እውቀትን በማሳደግ አቅምን ማጎልበት**

በልዩ ልዩ ወቅታዊና ሀገራዊ የኮሚሽኑ አጀንዳዎች ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ግንዛቤ ለመፍጠር እና ጋዜጣዊ መግለጫዎች ለመስጠት ታቅዷል፡፡

የኮሚሽኑን የሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም መረጃዎች ተደራሽ በማድረግ የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን የማስፈን ስራ ይከናወናል፡፡

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. የተዘጋጁ የሩብ ዓመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ሰነዶች
2. ለኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች እና ለተጠሪ ተቋማት የተደረገ ድጋፍና ክትትል
3. በመልካም አስተዳደርና ስነ-ምግባር የተፈጠረ ግንዛቤ
4. መመሪያን የተከተሉ ቀልጣፋ የፋይናንስ አገልግልቶችና ወቅቱን የጠበቁ የፋይናንስ ሪፖርቶች

5. የተዘጋጁ የኦዲት ሪፖርቶች
6. የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት
7. የተደራጀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃ
8. የጎለበተ የህዝብ ግንኙነትና የኮሚኒኬሽን ስራዎች

## ስትራቴጂክ ግብ 2፡- ኢኮኖሚውን በረዥም ጊዜ ዕይታ በመምራት ፈጣን ፍትሐዊና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማገዝ፤ (ክብደት 12)

### ተግባር 1፡- የጥናት ውጤቶችን የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮዎችን እና ታሳቢዎች ላይ መሰረት በማድረግ የልማት አማራጮችን በማዳበር በዘርፎች ትስስሮችን በመፍጠር የ30 ዓመት የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት

1.1 ለልማት ዕቅዱ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ

1.2 የጥናት ውጤቶችንና የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮዎችን ማሰባሰብና መቀመር

1.3 የተገኙ ተሞክሮዎችን የመጀመሪያ ረቂቅ በማዘጋጀት ግብዓት መሰብሰብና በዘርፎች መካከል የተቀናጀ እና በስፓሻል የተመጣጠነ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት

1.4 በአህጉራዊ፣ በቀጠናዊ በጐረቤት ሀገሮች ያሉ ለውጦችን እና የተደረሰባቸው ልዩ ልዩ ስምምነቶች በዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ

### ተግባር 2፡- ሀገራዊ የተቀናጀና የተመጣጠነ እና የስፓሻል እና ቀጠናዊ ትስስርን የሚያጎለብት የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ፣ ማኑዋል እና ቼክሊስቶች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ማዘጋጀት

2.1 ሀገራዊ የተቀናጀና የተመጣጠነ እና የስፓሻል እና ቀጠናዊ ትስስርን የሚያጎለብት የልማት ዕቅድ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

2.2 የሚዘጋጀውን ሀገራዊ የተቀናጀና የተመጣጠነ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ማኑዋል ማዘጋጀት

2.3 የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ቼክሊስቶችን ማዘጋጀት

### ተግባር 3፡- የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የኢኮኖሚ፣ የመሰረተ ልማት፣ የሰው ሀብት ልማት፣ የመልካም አስተዳድርና የሰላም ዘርፎችን ያካተተ ሀገራዊ የአንድ አመት እና ሶስት አመት የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት

3.1 ከ2014-2016 በጀት ዓመት በሶስት ዓመታት የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት

3.2 ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የመጀመሪያ ረቂቅ ማዘጋጀት

3.3 የተዘጋጀዉን ረቂቅ በዉይይት ማዳበርና የመጨረሻ የ3 ዓመት የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት

3.4 ከዘርፎች የፕሮግራም በጀትና ውጤት ጋር የተጣጣመ የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት

### ተግባር 4፡- የማክሮ ኢኮኖሚውን፣ሌሎች ዘርፎችን ሀገራዊ እና አለማቀፍ ሁኔታዎችን በመከታተል የ2014 እና የ3 ዓመት (2014-2016) በጀት ዓመት ያለውን የማክሮ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

ቀጣይ የሀገሪቱን እና ዓለማቀፋዊ ኢኮኖሚ ሀኔታዎችን በመገምገም የ2014 በጀት ዓመት እና ከ2014 እስከ 2016 በጀት ዓመት ያለውን የ3 ዓመት ማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡

### ተግባር 5፡- የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ማስተግበሪያ ስልቶች ተጨማሪ ሰነድ ማዘጋጀት

5.1፡ የሰው ሃብት ልማት ዕቅድ ሰነድ ማዘጋጅት

5.2፡ ለልማት ዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚሆን የፋይናንስ ፍላጎት በወጪ መጠንና በምንጭ እንዲሁም በዶላርና በብር መለየትና ማዘጋጅት

5.3፡ የልማት ፕሮጀክቶች ኢንቨሎፕ ማዘጋጀት

**ተግባር 6፡- በልማት ዕቅድ፣ በልማት ፕሮግራም ቀረጻ እና ለልማት ዕቅድ በሚያገለግሉ ስልቶች ላይ ለተቋሙ ባለሙያዎች፣ ለፌደራል አስፈጻሚ ባለሙያዎች እና ለክልሎች ስልጠና መስጠት እና የ10 ዓመቱን እቅድ ማስተዋወቅ**

6.1፡ በልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ በልማት ፕሮሮግራም ቀረጻ እና ለልማት ዕቅድ በሚያገለግሉ ስልቶች ላይ ለተቋሙ ባለሙያዎች፣ ለፌደራል አስፈጻሚ ባለሙያዎች እና ለክልሎች ስልጠና መስጠት

6.2፡ የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱን ማስተዋወቅ

**ተግባር 7፡-የማክሮ ኢኮኖሚውን ወቅታዊ ሁኔታ በየጊዜው በመከታተል መንግስትንና ባለድርሻ አካላትን ማሳወቅ**

**7.1 የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና ዋና ግቦች አፈጻጸምን የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት**

ለማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የሚዘጋጅ የ2013 በጀት ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም ግምገማ የሚያሳይ ሪፖርት ለማዘጋጀት፣ ለማሳተምና ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ታቅዷል፡፡

**7.2 የ2014 የየሩብ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት**

የ2014 በጀት ዓመት የሦስት ሩብ ዓመቶች (የመጀመሪያው፣ የሁለተኛውና የሦስተኛ ሩብ ዓመታት) የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ፡፡

**7.3 በኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ለውጥ አዝማሚያዎችን ላይ ጥናት ማከናወን**

በሀገራዊ ኢኮኖሚው እንቅስቃሴና የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለመዳሰስ በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ዙሪያ ጥናት ማካሄድን ይመለከታል፡፡

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. የተዘጋጀ ሀገራዊ የ30 ዓመት የልማት ዕቅድ
2. የተዘጋጀ የስፓሻል እና ቀጠናዊ ትስስርን የሚያሳልጥ የልማት ማዕቀፍ
3. የተዘጋጀ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ
4. የተዘጋጀ የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የአጭር ዘመን የልማት ዕቅድ እና የ3 ዓመት (2014-2016) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ
5. የተዘጋጀ የ2014 በጀት ዓመት እና ከ2014-2016 በጀት ዓመት ያለው የ3 ዓመት ማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ
6. የተዘጋጀ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ማስተግበሪያ የሰው ሀብት ልማት ዕቅድ ሰነድ እና የፋይናንስ ፍላጎት ዕቅድ ሰነድ
7. በልማት ዕቅድ፣ በልማት ፕሮሮግራም ቀረጻ እና ለልማት ዕቅድ በሚያገለግሉ ስልቶች ላይ የተገነባ አቅም
8. የ10 ዓመቱን እቅድ ለማስተዋወቅ የተካሄዱ መድረኮች

9. የተዘጋጀ፣ የታተመና ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ሰነድ
10. የተዘጋጀና የተሠራጩ የ2014 በጀት ዓመት የሶስት ሩብ ዓመት የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ሰነዶች
11. በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ዙሪያ የተካሄደ የጥናት ሰነድ

## ስትራቴጂክ ግብ 3፡- ብሔራዊ የልማት ዕቅድንና የልማት ፕሮጀክቶችን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)

ዋና ዋና ተግባራት

**ተግባር 1፡- የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የማክሮ እና የዘርፍ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በመገምገም የተጠቃለለ የአምስት ዓመት አገራዊ የግምገማ ሪፖርት በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቅጅዎች በገለልተኛ አማካሪዎች በመታገዝ ማዘጋጀት**

1.1 ገለልተኛ አማካሪዎቹን ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግና አስፈላጊ መነሻ ሪፖርቶችን ዝግጁ ማድረግ

1.2 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የማጠናቀቂያ ዘመን ረቂቅ ሪፖርት ማዘጋጀት

1.3 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የማጠናቀቂያ ዘመን ረቂቅ ሪፖርት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በአስተያየት ማዳበርና የመጨረሻ ረቂቅ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅጅ ሪፖርት ማዘጋጀት

**ተግባር 2፡- የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የተቀናጀና ወጥ የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት**

2.1 የኢኮኖሚ ዘርፎች የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት

2.2 የማህበራዊ ዘርፎች የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲሁም የስርዓተ ምግብ ጉዳይ፣ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ እና ሌሎች የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች መካተታቸውን ማረጋገጥ

2.3 የመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት

2.4 የመካከለኛና ትላልቅ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ደረጃ የሚያሳይ የ2013 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት

**ተግባር 3፡- የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በክልል እና በፌደራል ደረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ማዘጋጀት**

3.1 ለየአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ 2013 በጀት ዓመት የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በክልል እና በፌደራል ደረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለሚደረግ ምክክር አስፈላጊውን በጀት፣ ገለጻ እና መርሀግብር ማዘጋጀት

3.2 በተዘጋጀው መርሀግብርና ቅድመ ዝገጅት መሠረት ምክክሩን በክልልና በፌደራል ደረጃ ማካሄድ

ተግባር 4፡- በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት ትግበራ ወቅት ደካማ አፈጻጸም ባሳዩ በተመረጡ ፕሮግራሞች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ

4.1 በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የጤና ዘርፍ ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መስክ ምልከታ በማካሄድ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ

4.2 በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የኢኮኖሚ ዘርፎች ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ መስክ ምልከታ በማካሄድ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ

4.3 በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የመልካም አስተዳደርና የሰላም ዘርፍ ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በተመረጡ አካባቢዎች ላይ መስክ ምልከታ በማካሄድ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ

4.4 የመካከለኛና ከፍተኛ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በመስክ መመልከትና ድጋፍ ማድረግ

**ተግባር 5፡- የኢኮኖሚ ዘርፎችን (የግብርናና የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፣ የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ እንዲሁም የማዕድንና ነዳጅ) ዘርፎችን የ10 ዓመቱ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም መከታተል**

5.1 የኢኮኖሚ ዘርፎችን የ2014 በጀት ዓመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚያስችል ቼክ ሊስት ማዘጋጀት

5.2 የኢኮኖሚ ዘርፎች የ2014 በጀት አመት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የአፈፃፀም መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት

5.3 የኢኮኖሚ ዘርፎች በየዓመቱ እያስመዘገቡ ያለውን ውጤት ማሳየት፣ ክፍተቶችን መለየት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማገናዘብ፣ የስትራቴጂዎችን አተገባበር መለየትና ምክረ ሃሳብ ማቅረብ

5.4 የተጠቃለለ የኢኮኖሚ ዘርፎች የ2014 በጀት አመት የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት

**ተግባር 6፡- ከመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት Baseline እና Target የሌላቸው የአፈጻጸም አመልካቾች እንዲሟሉ ማድረግ**

**ተግባር 7፡- የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ፕላን የአፈጻጸም አመልካቾችን ማዘጋጀት**

**ተግባር 8፡- የመካከለኛና ከፍተኛ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ደረጃ የሚያሳይ የሩብ ዓመት የተጠቃለለ ሪፖርት ማዘጋጀት**

**ተግባር 9፡- በመሠረተ ልማትና በልማት ፕሮጀክቶች ፕላን አፈፃፀም ዙሪያ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ**

9.1 በልማት ፕሮጀክቶች፣ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን እና በመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ፕላን አፈፃፀም ዙሪያ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ

9.2 በልማት ፕሮጀክቶች፣ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን እንዲሁም በመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ፕላን አፈፃፀም በየጊዜው በመከታተልና በመገምገም ግልፅኝነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ ተሞክሮዎችን መቀመርና ተደራሽ ማድረግ

9.3፡- የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን ፕላን አፈፃፀምን ክትትልና ግምገማ ስርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ተደራሽ ማድረግ

**ተግባር 10፡- የዘላቂ የልማት ግቦችን እና የአፍሪካ አጀንዳ 2063 አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. በገለልተኛ አካል (አማካሪዎች) የተዘጋጀ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የተጠቃለለ የአምስት ዓመት አፈጻጸም ግምገማ የአማርኛ እና እንግሊዥኛ ቅጅ ሪፖርት
2. የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት
3. የአስር ዓመቱ (2013-2022) የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት የትግበራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በክልል እና በፌደራል ደረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተዘጋጀ ምክክር
4. በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የ2013 በጀት ዓመት ትግበራ ወቅት ደካማ አፈጻጸም ባሳዩ በተመረጡ ፕሮግራሞች ዙሪያ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት
5. የዘላቂ የልማት ግቦችን እና የአፍሪካ አጀንዳ 2063 አፈጻጸም ሪፖርት
6. የተዘጋጀ የኢኮኖሚ ዘርፎች የ 2014 ዓ.ም ክትትልና ግምገማ ሪፖረት
7. ለዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በየተሰጠ የቴክኒክ ድጋፍ
8. የተሟላ ቤዝላይን እና ታርጌት ያለው የአፈጻጸም አመልካች
9. የተዘጋጁ KRAs & KPIs

## ስትራቴጂክ ግብ 4፡- በተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የግምገማ ጥናት ማካሄድ፤ (ክብደት 7)

**ተግባር 1፡- በተመረጡ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የፋይዳ ግምገማ (Impact Evaluation) እንዲካሄድ ማድረግ**

ሀገራችን በከፍተኛ ወጪ ተነንብተው በትግበራ ላይ የሚገኙ የመሠረተ ልማትና የልማት ፕሮጀክቶችን የአጋማሽ ዘመን ግምገማ፣ የመጨረሻ ዘመን ግምገማና የፕሮጀክቶቹን የስኬትና ፋይዳ ግምገማ ማከናወንና ያመጡትን ተደራሽነት በራስና በገለልተኛ አካል ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥናት ለማካሄድ ታቅዷል፡፡

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

10. በተመረጡና ተጠናቀው ወደ ስራ በገቡ የልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የተካሄደ የግምገማ ጥናት ሪፖርት

## ስትራቴጂክ ግብ 5፡- ብሔራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅትና የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)

**ተግባር 1፡- በዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን**

1.1 ለሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ግብዓት የሚሆን ጥናት ማካሄድ

1.2 ለሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ጥናት መሠረት የአቅም ግንባታ ጉዳዮችን መለየት

1.3 በዳሰሳ ጥናት በተለዩ የአቅም ግንበታ ጉዳዮች መሠረት የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን

**ተግባር 2፡- የዲጅታል ክትትና ሪፖርት ሥርዓትን (Digital Monitoring and Reporting Systeme software) ለመተግበር የለማውን ሶፍትዌር አሰራሩን በቅርብ መከታተልና የበለጠ እንዲሻሻል ማድረግ**

**ተግባር 3፡- ለኮሚሽኑና ለአስፈፃሚ ተቋሟት ባለሙያዎች በImpact evaluation methods ላይ ስልጠና መስጠት**

**ተግባር 4፡- ለተመረጡ የግል ድርጅቶች የInvestment analysis/management ስልጠናዎችን መስጠት**

**ተግባር 5፡- ለዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት**

5.1 ከማህበራዊ ዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ተናቦ በመስራት ቴክኒካዊ የምክር አገልግሎት በመስጠት ድፋግ ማድረግ

5.2 ከመልካም አስተዳደርና ሰላም ዘርፍ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በክትትልና ግምገማ ስራ ላይ ለሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት

**ተግባር 6፡- የፌዴራል ተቋማትን የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ አሰራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል በዳሰሳ ጥናት መለየትና ድጋፍ ማድረግ**

**ተግባር 7፡- ሀገራዊ የፕሮጀክቶች የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥልጠና ማዘጋጀት**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. በዳሰሳ ጥናት ላይ ተመስርቶ የተጠናከረና የተገነባ ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ አቅም
2. ውጤታማ የዲጅታል ክትትና ሪፖርት ማቅረቢያ ሥርዓት (Digital Monitoring and Reporting Systeme software) ሶፍትዌር
3. የተሰጡ የቴክኒክ ድጋፎች

## ስትራቴጂክ ግብ 6፡- የልማት ዕቅድ ዝግጅት ከጥናትና ምርምር ጋር ያለውን ትስስር ማሳደግ፤ (ክብደት 8)

**ተግባር 1፡- ለልማት ዕቅድ ግብዓት የሚሆኑ በማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ዙሪያ እና ቀጠናዊ እና አካባቢያዊ ትስስር፣ ትብብርና አጋርነት የሚያረጋግጡ ጥናቶችን ማካሄድ**

1.1 በሰራተኛው ምርትና ምርታማነት (Labor Productivity) ላይ ጥናት ማከናወን

1.2 በኢኮኖሚ በአምራች ዘርፎች የምርት ሰንሰለት ላይ እንዲሁም የገበያና የአምራች ዘርፎች ቁርኝት ላይጥናት ማድረግ

1.3 በኢኪኮኖሚው መዋቅራዊ ሽግግር ሂደት እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች፣ እድሎችና መከተል ያለብን ዓቅጣጫዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን

1.4 ለቀጠናዊና አካባቢያዊ ትስስር፣ ትብብርና አጋርነት የሚያግዙ ጥናቶችን ማከናወን

**ተግባር 2፡- የድህነትና የኑሮ ደህንነት ትንተና ሥራ ማካሄድ**

## 2.1 በsurvey data management, በUni-dimentional and multi-dimentional የድህነት ትንተና ዘዴዎች ዙሪያ ሥልጠና መስጠት

የኮሚሽኑን እና የሌሎች ተቋማትን ባለሙያዎችን እንዲሁም በክልሎች የሚገኙ ባለሙያዎችን ለድህነት ትንተና ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን (በተለይም HCES and WMS) በሚመለከት እንዴትና በምን መልኩ ማደራጀትና መጠቀም እንደምቻል ለማሳወቅ በተጨማሪ በድህነት ትንተና ዙሪያ የባለሙያዎች አቅም የበለጠ ማጠናከር ታስቧል።

## 2.2 የድህነት መስመር (Poverty line) ለመገመት የምንጠቀምበት የምግብ ፍጆታ ቅርጫት (consumption basket) በመፈተሽ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ

ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የድህነት ትንተና ሥራዎች በዋናነት መሰረት ያደረጉት እኤአ በ2002 የተዘጋጀውን የምግብ ፍጆታ ቅርጫት (consumption basket) መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም የሰዎች የፍጆት ሁኔታ (consumption pattern) በጊዜው በሚከሰቱ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ኢኮኖሚያዊ ባልሆኑ ምክንያቶች የባህሪይ ለውጦች እንደሚኖሩ የሚገመት በመሆኑ ወቅታዊ የፍጆታ ሁኔታን መሰረት ያደረገ የድህነት መስመር ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ በ2014 በጀት ዓመት የድህነት መስመር (Poverty line) ለመገመት የምንጠቀምበት የምግብ ፍጆታ ቅርጫት (consumption basket) በመፈተሽ ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ታቅዷል።

## 2.3 ስድስተኛውን ሀገር አቀፍ የልማትና የድህነት ትንተና ሪፖርት ማዘጋጀት

የመንግስት የድህነት ቅነሳ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ውጤታማነት ለመከታተልና ለመገምገም እንዲቻል በየአምስት ዓመቱ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ እና የኑሮ ደህንነት ሁኔታ የመስክ የናሙና ጥናቶች የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አምስት ተከታታይ የልማትና የድህነት ትንተና ጥናት ሪፖርት ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። በተመሳሳይ ስድስተኛውን የልማትና የድህነት ትንተና የጥናት ሪፖርት ሰነድ ለማዘጋጀት እንዲቻል በበጀት ዓመቱ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ።

## 2.4 ሀገራዊ የፈርጀ ብዙ የድህነት አመልካች/Multidimension Poverty Index/ የድህነት ትንተና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት

ድህነትን በሁሉም ገጽታው ለመለካት፣ ለመተንተን፣ ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ድህነት ካለው የገቢ ገጽታ ባሻገር ፈርጀ ብዙ ገጽታውን የሚለካ የድህነት ትንተና ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ይህን ለማከናወን በ2013 በጀት ዓመት የተጀመረውን ሀገራዊ የዘርፈ ብዙ የድህነት አመልካች (MPI) የቅድመ ዝግጅት ቀሪ ሥራ በበጀት ዓመቱ በማጠናቀቅ ሀገራዊ የፈርጀ ብዙ የድህነት ትንተና ሪፖርት ሰነድ (E-MPI) ይዘጋጃል።

## 2.5 የድህነት ትንተና አተገባበር የአፈፃፀም ማኑዋል ማዘጋጀት

የድህነት ትንተና ሥራ ከመረጃ መሰብሰብ እስከ መጨረሻ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ የራሱ የሆነ ሳይንሳዊ አካሄድ ያለው በመሆኑ ይህንን ሂደት ባልተዛደለ መልኩ ጠብቆ ለማስካሄድና በቀጣይ ወደ ኮሚሽኑ የሚመጡ ባለሙያዎችና የተለያዩ አካላት በጉዳዩ ዙሪያ ግልጽ አካሄድ እንድኖራቸው ለማስቻል የአሠራር ሥርዓቱን ሂደቱ የሚያሳይ ማኑዋል ማዘገጃት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት ይሄን ተግባር ለማከናወን ታስቧል።

**ተግባር 3፡- በኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ በ2014 ዓ.ም ጥናት ሊካሄድባቸው የሚገባ የጥናት መስኮችን በመለየት ጥናቶችን ማካሔድ**

**ተግባር 4፡- የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚመለከት አለማቀፋዊ ፣አህጉራዊ፣ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችን እና በዘርፍ ላይ ያሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማሰባሰብና ትርጉም ባለው መልኩ ማደራጀት**

**ተግባር 5፡- የአጀንዳ 2063 አፈፃፀም ሪፖርትን ጨምሮ የማህበራዊ ዘርፍ ፕላን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ዘርፎች (የጤና፣ ትምህርት እና የማሕበራዊ ጉዳይ እና የሴቶች ህፃናት እና ወጣቶች) ተያያዥ ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳ መረጃዎችን (time series data) ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ ማዘጋጀትና መጠቀም እንዲሁም በሚጠየቅበት ጊዜ መረጃ መስጠት**

**ተግባር 6፡- ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር የአገራዊ የግምገማ አቅም ዳሰሳ ጥናት ማስተባበር**

**ተግባር 7፡- ብሔራዊ የሰው ሀብት ልማትና የስራ ገበያ ግምገማዊ ጥናት (National human capital development and labour market evaluation study) ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጥናት ማድረግ**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. በድህነት ትንተና ዘዴዎች ዙሪያ የተሰጡ ሥልጠናዎች
2. የተዘጋጀ ስድስተኛው ሀገር አቀፍ የኑሮ ደህንነትና ድህነት ትንተና /Consumption based/ ሪፖርት ሰነድ
3. የተዘጋጀ ሀገራዊ የፈርጀ ብዙ የድህነት አመልካች /MPI/ የድህነት ትንተና ሪፖርት ሰነድ
4. የድህነት መስመር ለመገመት የምንጠቀምበት የምግብ ፍጆታ ቅርጫት ለማሻሻል የቀረበ ምክረ ሃሳብ
5. የተዘጋጀ የድህነት ትንተና አተገባበር የአፈፃፀም ማኑዋል
6. በኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚመለከት የጥናት ሰነድ
7. የተደራጀና ጥቅም ላይ የዋለ የሰው ሀብት ልማት እና የስራ ስምሪት ዘርፍ ተያያዥ ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳ መረጃዎችን
8. የተዘጋጀ የአገራዊ የግምገማ አቅም ዳሰሳ ጥናት ሰነድ
9. የተዘጋጀ ብሔራዊ የሰው ሀብት ልማትና የስራ ገበያ ግምገማዊ ጥናት (National human capital development and labour market evaluation study) ሰነድ

## ስትራቴጂክ ግብ 7፡- ፖሊሲዎችና የልማት ዕቅዶች በመረጃና በትንታኔ ላይ የተመረኮዙ እንዲሆኑ ማድረግ (ክብደት 8)

**ተግባር 1፡- በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በድህነትና የኑሮ ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት ማካሄድ እና ወቅታዊና ሁሉን አቃፊ የሆኑ ሐገራዊ የኢኮኖሚ ሞዴሎችን መቅረጽ**

### 1.1 ሀገራዊ የሶሻል አካውንቲንግ ሜትሪክስን ዝግጅት ሪፖርት ማዘጋጀት

የማህበራዊ አካውንቶች መካከል የግብዓት፣ የምርት የገቢ ሥርጭት ትስስርን የሚያሳይ ሀገራዊ የሶሻል አካውንቲንግ ሜትሪክስን (social accounting matrix) ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በቀጣይ የዝግጅቱን ሂደት እና አጠቃላይ ስራውን የሚያካትት ሪፖርት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

**1.2 ሲስተምስ ዳይናሚክስ ሞዴል (Systems Dynamics Model) ዝግጅት ሪፖርት ማዘጋጀት**

የኢኮኖሚ መዋቅሮችን፣ ባህሪያቸውን እና እርስ በእርስ ያላቸውን ግብረ-መልሳዊ ትስስር ባረጋገጠና የአየር ንብረት ለውጥን በማካተት መልኩ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚያሳይ ሀገራዊ የሲስተምስ ዳይናሚክስ ሞዴል (systems dynamics model) የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ የዝግጅቱን ሂደት እና አጠቃላይ ስራውን የሚያካትት ሪፖርት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

**1.3 የማክሮ ኢኮኖሜትሪክ ሞዴል ማዘጋጀት**

የሀገሪቱን የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታና ፖሊሲ ትንተና የሚያገለግል ሀገራዊ የማክሮ ኢኮኖሜትሪክ ሞዴል ማዘጋጀትን፣ ማፀደቅንና ማስፋፋትን ያካትታል፡፡

**የሚጠበቁ ውጤት**

1. የተዘጋጀ ሶሻል አካውንቲንግ ማትሪክስ (SAM) ሪፖርት
2. የተዘጋጀ የሲስተምስ ዳይናሚክስ ሞዴል (systems dynamics model) ሪፖርት
3. የተዘጋጀ የማክሮ ኢኮኖሜትሪክ ሞዴል

## ስትራቴጂክ ግብ 8፡- የመንግስት ኢንቨስትምንት (ፕሮጀክቶች) አስተዳደር እና አመራር ውጤታማነትን ማሻሻል፤ (ክብደት 10)

**ተግባር 1፡- የፌደራል መንግስት ፕሮጀቶችን ላይ ግምገማ በማከናወን ምክረ ሀሳብ ማቅረብ**

1.1 የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ማንዋሎች እና ቅፆችን ማሻሻል

1.2 በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ በማከናወን ምክረ ሀሳብ ማቅረብ

1.3 የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ የቀረበባቸውን ፕሮጀክቶች በመገምገም ምክረ ኃሳብ ማቅረብ

1.4 በፕሮጀክቶች አዋጭነት ጥናት ዝግጅት እና የቅድመ ትግበራ ግምገማ ላይ የአሰልጣኖች ስልጠና መስጠት

1.5 በፌደራል መንግስት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርዓት እና በፕሮጀክቶች የፅንሰ ሀሳብ እና የአዋጭነት ጥናት እና ግምገማ ላይ የግንዛቤ መስጫ መድረኮች ማከናወን

**ተግባር 2፡- የተሻሻለ የፕሮጀክቶች የኢኮኖሚ መለወጫ እና መመዘኛ መመሪያ (Standard Economic Converstion Factor and Parameter)**

2.1 ፕሮጀክቶች የኢኮኖሚ መለወጫ እና መመዘኛ መስፈርት አሁን ካለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና ማህበራዊ ለውጦች አንፃር አስፈላጊነት ላይ አጭር ዳሰሳ ማዘጋጀት

2.2 የተዘጋጀውን ቢጋር በአማካሪ እንዲገመገም ማድረግ

2.3 ለመስፈርቱ ዝግጅት እና ውቅታዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ማሰባሰብ

2.4 የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የተሻሻለ ፕሮጀክቶች የኢኮኖሚ መለወጫ እና መመዘኛ መስፈርት ማዘጋጀት

**ተግባር 3፡- የ10 ዓመት የልማት እቅድን ለማስፈፀም የመንግስት የኢንቨስትመንት ፕላን ማዘጋጀት (Public Investment Resource Envelope Plan)**

3.1 የኢንቨስትመንት ፕላን የዝግጅት ወሰን፤ ምን ይዘቶችን እንደሚይዝ እና የዝግጅት አግባብ የሚያሳይ የስራ መዘርዝር ማዘጋጀት

3.2 በተዘጋጀው ቢጋር ላይ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር ምክክር በማድረግ ቢጋሩን ማዳበር

3.3 የኢንቨስትመንት ፕላን ዝግጅት መሰረታዊ ይዘቶችን የሚያሳይ ማንዋል ማዘጋጀት

3.4 ሴከተር መስሪያ ቤቶች የኢንቨስትመንት ፕላን በሚዚጋጁበት ወቅት ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ

3.5 ከሴክተሮች የተዘጋጀውን የኢንቨስተመንት ፕላን መሰረት በማድረግ ወጥ የሆነ ከሀገራዊ ማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች ጋር የተጣጣመ የኢንቨስመንት ፕላን ማዘጋጀት

**ተግባር 4፡- በተመረጡ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ማንዋል ማዘጋጀት**

4.1 የሴክተር ማንዋል ዝግጅት ስራ መዘርዝር ማዘጋጀት

4.2 ለሴክተር ፕሮጀክቶች ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባበሰብ

4.3 የመጀመሪያ ረቂቅ ሴክተር ፕሮጀክቶች ማንዋል መዘጋጀት

4.4 በአስተያየት የዳበረ የሴክተር የፕሮጀክት ዝግጅት ማንዋል ማዘጋጀትመረጡ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ማንዋል ማዘጋጀት

**ተግባር 5፡- ለፕሮጀክቶች የአዋጭነት ዝግጅት ግብዓት የሚያገለግል የፕሮጀክት የግብዓት እና የዋጋ መረጃ ቋት ማዘጋጀት**

5.1 ለፕሮጀክቶች ዝግጅት እና አዋጭነት ጥናት የሚያገለግሉ መረጃዎችን መለየት

5.2 የተለዩ መረጃዎች የሚጠናከሩበትን የመረጃ ቋት አማራጭ መለየት

5.3 የተለዩ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ ማደረጃት

5.4 የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንዲሁም መረጃዎችን በቀላሉ ተደራሽ የሚያደርግ የፕሮጀክት ዝግጅት እና አዋጭነት ጥናት መረጃ ቋት መዘርጋት

**ተግባር 6፡- በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር ስርዓት ላይ ስልጠና ማዘጋጀት**

**ተግባር 7፡- የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶችን አስተዳደር እና አመራር አዋጅ ደንብን ማዘጋጀት**

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. አዋጭነታቸው ተረጋግጠው በበጀት ላይ የተተከሉ የመንግስት ፕሮጀክቶች

2. በፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ ላይ የተሰጡ ስልጠና
3. በመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርዓት ላይ ግንዛቤያቸው የጎለበተ ባለድርሻ አካላት
4. ወቅታዊ የተደረገ የመለወጫ መስፈርት
5. የተዘጋጀ የመንግስት ፕሮጀክቶችን በቅደም ተከተል ለመለየት የሚያስችል የኢንቨስትመንት ፕላን
6. የተዘጋጀ የ3 ሴክተሮች የፕሮጀክት ዝግጅት እና አዋጭነት ጥናት መመሪያዎች
7. የፕሮጀክቶች የግብዓት እና የዋጋ የመረጃ ቋት
8. በመንግስት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና አመራር ላይ የተሰጠ ስልጠና
9. የተዘጋጀ የደንብ ሰነድ

## ስትራቴጂክ ግብ 9፡- የብሔራዊ ኢኮኖሚ አመላካች መረጃዎችን ማመንጨትን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)

**ተግባር 1፡- እየተሰሩ ያሉትን የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንቶችን ማዘጋጀት እና ሥርጭትን ማሻሻል**

1.1 የ 2013 በጀት ዓመት የሀገር ውስጥ ምርት ከአቅርቦት አንጻር (Supply side GDP) እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side) GDP) ትመና አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብና በማጠናቀር (በመገመት) ለተጠቃሚዎች ማቅረብ

1.2 የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት አመታዊ ሪፖርት ከሚይዘዉ መረጃ በተጨማሪ የትንተና ሪፖርት (Analytical report) ማዘጋጀት።

1.3 የ2008 ቋሚ በጀት ዓመት መሠረት የረጅም ዘመን የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃዎች (National Accounts Time Series Data) ማዘጋጀት

1.4 የዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ግመታ በቋሚ ዋጋ ከአጠቃቀም አንፃር (GDP by Expenditure at constant price) ማዘጋጀት

1.5 የዓመታዊ ሀገራዊ ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (Supply side GDP) እና ከአጠቃቀም አንፃር (Expenditure Side) ጊዜያቸውን ጠብቀው የተከለሱ መረጃዎች ለመንግስትና እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት

**ተግባር 2፡- ተጨማሪ የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንቶችን ማዘጋጀት**

2.1 የ2013 4ኛ ሩብ ዓመት እና የ2014 ሩብ ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (QGDP - Supply side) ማዘጋጀት።

2.2 የሀገር ውስጥ የሩብ አመት ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (QGDP - Supply side) የመረጃ ሽፋን፣ ጥራት፣ ወቅታዊነት እና አስተማማኝ ሆነዉ በተገኙ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ የአገማመት ዘዴ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ Gap Assessment እና መረጃዎችን ማሰባሰብ።

2.3 ተሻሽሎ የቀረበ አዲስ የሩብ አመት ምርት የአገማመት ዘዴ መመሪያ ከአቅርቦት አንጻር (Quarterly Sources and Methods manual) ማዘጋጀት።

2.4 የሀገር ውስጥ የሩብ አመት ምርት ግመታ ከአቅርቦት አንጻር (QGDP - Supply side) በተሻሻለ የመረጃ ምንጭ አዲስ የግመታ ውጤቶችን ለተጠቃሚ ማቅረብ።

**ተግባር 3፡- የክልል ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት ሥርዓት መዘርጋት እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሥራት**

3.1 የብሔራዊ /ክልላዊ ኢኮኖሚ አካውንት አዘገጃጀት መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ሥልጠና መስጠት፡፡

3.2 የክልል ኢኮኖሚ አካውንት በተመለከተ ድንበር ተሻጋሪ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ክልላዊ ግምት የማዘጋጀትና የማከፋፈል (Allocation of trans regional /cross border economic activities) ሥራዎችን ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋራ የጋራ መግባበት ላይ መድረስ፡፡

3.3 የክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃዎች ከብሔራዊ አካውንት አሠራር ስርዓት ጋር በተጣጣመና ደረጃውን የጠበቀ የክልል አካውንትን አሰራር ስርዓት በተቀናጀ መልኩ ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ከክልሎች ጋር ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጎልበት፣ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ማስተባበር፡፡

3.4 የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት አሠራር መመሪያ ማጠናቀቅ

3.5 የክልል አካውንትን ስርዓት ዝርጋታ አሁን ካቀረቡት በተጨማሪ ክልሎች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ

3.6 በብሔራዊና በክልል ደረጃ የሚቀነባበሩ የክልል ኢኮኖሚ አካውንት መረጃዎች በማዕከላዊነት ተደራጅተው ለየክልሉ እና ለከተማ መስተዳደሮች ማጋራት፡፡

3.7 የክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች ኢኮኖሚ አካውንት የሙከራ የግመታ ስራዎች በጋር validation መስራት፡፡

## ስትራቴጂክ ግብ 10፡- የስነ ህዝብ ባህሪያትን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር እንዲጣጣም ማገዝ፤ (ክብደት 10)

### ተግባር 1፡- ለሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ፣ ለልማት ዕቅዶች ግብአት የሚሆኑ ጥናቶችን እና የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ክለሳ ማካሄድ

1.1 አሁን ባለው የሥነሕዝብ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ የፖሊሲ መግለጫ ጥናቶችን ማካሄድና ውጤታቸውን ማስተዋወቅ

1.2 በእውነተኛ መረጃ ላይ የተመሰረቱ እና ለሥነሕዝብ ፖሊሲ ክለሳ ግብአት የሚሆኑ በወጣቶች ፍልሰት፣ ሥራ አጥነትና እና በሥነሕዝብ ትርፍ ድርሻ ላይ ጥናቶችን ማካሄድ

1.3 በሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ትግበራ ዳሰሳ ጥናት ውጤት ምክረ ሃሳብ መሰረት በ1985 ዓ.ም የወጣውን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲን ክለሳ ጥናት ማድረግ፣ ማፀደቅ እና ማስተዋወቅ

1.4 በሥነ ሕዝብ ጉዳይ ላይ ለአሁንና ለወደፊት ማጠቀሻ ሆኖ እንዲያገለግል እና የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት እንዲቻል ከዚህ በፊት የሥነሕዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ እንዲያገለግል ተዘጋጅቶ የነበረውን ሞጁል ወቅቱን ባገነዘበ ሁኔታ መከለስ

### ተግባር 2፡- ለተለያዩ የስነ ህዝብ ጉዳዮች ግብአት የሚውሉ ሶፍትዌሮችንና መረጃዎችን በማሰባሰብ ተደራሽ ማድረግ

2.1 ለማኑዋል ዝግጅት ሶፍትዌር ግዢ ማከናወን

2.2 የሥነ-ሕዝብ መረጃዎችን የያዘ የ IEC/BCC ሰነድ ማሳተምና ማሰራጨት

2.3 በሥነ-ሕዝብና ልማት ዙሪያ ያሉ መረጃዎችን፣ ጥናቶችንና ሪፖርቶችን ማሰባሰብ

**ተግባር 3፡- የግንዛቤ ማዳበሪያና የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና እና የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት**

3.1 በሥነ ሕዝብ ዳይናሚክስ በዲሞግራፊ ሽግግር፣ በሥነ ሕዝብ ትርፍ ድርሻ እና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ ውስጥ ማካተት የሥነ ሕዝብ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ወርክሾፕ ማዘጋጀት

3.2 ከሚዲያና የኮሙኒኬሽን ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰቡ አነስተኛ ቤተሰብ አስቤን መተግበር ይችል ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጣ የኢንፎርሜሽን ትምህርትና ኮሙኒኬሽን እና የማህበረሰብ ባህሪ ለውጥና ኮሙኒኬሽን ተግባራትን ማካሄድ

3.3 ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሌሎች አጋር ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበበር አምስተኛውን አገር አቀፍ የሥነሕዝብና ልማት ኮንፈረንስ ማዘጋጀት

3.4 በፖሊሲ ማብራሪያ እና ለፖሊሲ ግብአት በተካሄዱ ጥናቶች ላይ የማህረሰብ ክርክር/ ውይይት ማካሄድ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

1. የፖሊሲ ክለሳ ግባት ጥናቶች እና ተከለሰ ፖሊሲ ሰነድ
2. የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን በሀገራዊ የልማት ዕቅዶች ለማካተት/ ለማስተሳሰር የሚያግዝ የተዘጋጀ ሶፍትዌር
3. የተሰባሰቡ፣የተደራጁና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሆኑ የሥነ ሕዝብ መረጃዎች
4. የተካሄዱ የግንዛቤ ማዳበሪያ እና የአቅም ማጎልበቻ መድረኮች

## ሠንጠረዥ 1፡- የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት፣ የዕቅድ መለኪያዎች እና የድርጊት መርሃ-ግብር

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| **የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን በወቅቱና በጥራት በማከናወን ለዋና ዋና አመታዊ የኮሚሽኑ ግቦች ትግበራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ (ክብደት 5)** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የእቅድ ዝግጅት | | | | 2 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ክ |
| 1.1 | የኮሚሽኑን የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ማዘጋጀት | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | | | | | | | | | | | | ተዘጋጅቶ የፀደቀ አመታዊ እቅድ | |
| 1.2 | የኮሚሽኑን የ2014-2017 በጀት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት | በቁጥር | | 1 | 1 | | | 1 | | | | | | | | | | ተዘጋጅቶ የፀደቀ ተቋሟዊ ስትራቴጂክ እቅድ | |
| 2 | የፈጻሚ ዝግጅት | | | | 7 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ክ |
| 2.1 | የኮሚሽኑን የሰው ሃብት በበጀት አመቱ መጨረሻ 250 ማድረስ | በቁጥር | 188 | 250 | 1 | | | 10 | | | 16 | | | 18 | | | 18 | | |
| 2.2 | ዘመናዊ የሰው ሀብት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሲስተም (ICSMIS) ተግባራዊ ማድረግ | በመቶኛ | 100 | 100 | 1 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | የተቀናጀ የሰው ሀብት መረጃ | |
| 2.3 | የአመራር እና ባለሙያ አቅም በረጅም፣ በመካከለኛ እና በአጭር ጊዜ ትምህርትና ስልጠና መገንባት | | | | 3 | | | | | | | | | | | | | አቅሙ የተገነባ የሰው ኃይል | |
| 2.3.1 | ለኮሚሽኑ ባለሙያዎች (የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ) የ2ኛ ዲግሪ (MA, MSc) እና የ3ኛ ዲግሪ (PhD) የትምህርት ዕድል ማመቻቸት | በቁጥር | | 6 | 1 | | | | | | | | | 6 | | | | | |

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| 2.3.2 | ከሥራ ክፍሎች የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የተገኘ መረጃን መሰረት በማድረግ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት | በቁጥር | | 70 | 1 | | | 10 | | | 20 | | | 20 | | | 20 | | |
| 2.3.3 | ቅድመ ሥራ ማስተዋወቂያ (Induction) ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለአዲስ ቅጥር ሰራተኞች ስልጠና መስጠት | በቁጥር | | 62 | | | | 10 | | | 16 | | | 18 | | | 18 | | |
| 2.3.4 | ለኮሚሽኑ ወጣት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የአቅም ግንባታ ስልጠና ማመቻቸት | በቁጥር | | 52 | | 27 | 25 | | | | | | | | | | | | |
| 2.4 | የኮሚሽኑን ሰራተኞች የውጤት ተኮር አፈጻጸም የተጠቃለለ ውጤት መረጃዎች አጠናክሮ መያዝ | በቁጥር | | 2 | 1 | | | | | | 1 | | | | | | 1 | የተጠቃለለ የሠራተኞች የውጤት ተኮር መረጃ | |
| 3 | የግብዓት ዝግጅት | | | | 4 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ክ |
| 3.1 | የኮሚሽኑን የ2013 አመታዊ የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት እና የ2014 በ.ዓ የስራ መርሃ-ግብር ማዘጋጀት እና ለገ/ሚ መላክ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | | | | | | | | | | | | የተዘጋጀ የስራ መርሃ-ግብር፣ የአፈፃፀም ሪፖርት እና የፕሮግራም በጀት ጥያቄ | |
| 3.2 | የኮሚሽኑን የ2014 በ.ዓ የየሩብ ዓመት የፕሮግራም በጀት አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለገ/ሚ መላክ | በቁጥር | | 3 | 1 | | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | | |
| 3.3 | የኮሚሽኑን የ2015 በ.ዓ | በቁጥር | | 1 | 1 | | | | | | | | | 1 | | | | | |

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| | የፕሮግራም በጀት ጥያቄ ማዘጋጀት እና ለገ/ሚ መላክ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3.4 | የኮሚሽኑን የ2014 በ.ዓ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እና ማፀደቅ | በቁጥር | | 1 | 1 | | | 1 | | | | | | | | | | የተዘጋጀ የግዥ ዕቅድ እና የአፈፃፀም ሪፖርት | |
| 3.5 | የኮሚሽኑን የ2014 በ.ዓ የሩብ ዓመት የግዥ ሪፖርት ማዘጋጀት | በቁጥር | | 3 | 1 | | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | | |
| **ስትራቴጂክ ግብ 1፡- የአሰራር እና የአገልግሎት አሠጣጥ ስርዓትን ማጎልበት፤ (ክብደት 10)** | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | የኮሚሽኑን የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ማጎልበት | | | 4 | 1 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | ተዘጋጅቶ የተገመገመ የአፈፃፀም ሪፖርት | ፕ.ል.ኮ |
| 2 | ለኮሚሽኑ የስራ ክፍሎች እና ለተጠሪ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግ | | | | 1 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ኮ |
| 2.1 | ለኮሚሽኑ የሥራ ክፍሎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | | 4 | 0.5 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | የተደረገ ድጋፍና ክትትል | |
| 2.2 | ለተጠሪ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | | 4 | 0.5 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | |
| 3 | የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራዎችን መከታተል | | | | 1 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ኮ |
| 3.1 | የኮሚሽኑን አመራርና ሰራተኞች ሃብትና ንብረት ማስመዝገብ | በቁጥር | 187 | 60 | | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | | |

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| 3.2 | ተቋሚዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 3.3 | በተዘጋጀው ተቋሚዊ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ላይ ለተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ስልጠና መስጠት/ግንዛቤ ማስጨበጥ | በቁጥር | | 1 | | | | | 1 | | | | | | | | | | |
| 3.4 | የስነ-ምግባር መመሪያ/ኮድ ተግባዊነትን መከታተል እና አስቸኳይ የሙስና መከላከል ተግባራትን ማከናወን | በመቶኛ | | 100 | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | | |
| 3.5 | ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን በመለየት ጥናት ማካሄድ እና የተለዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለመቅረፍ የሚሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ | በቁጥር | | 3 | | | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | | |
| 3.6 | ለኮሚሽኑ ሰራተኞች የስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስናን ስለመከላከል ስልጠና መስጠት | በቁጥር | | 6 | | | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | |
| 3.7 | የፀረ-ሙስና ቀንን ማክበር | በቁጥር | | 1 | | | | | | 1 | | | | | | | | | |
| 4 | የመንግሥት የፋይናንስ አሰራር ሥርዓትን በመከተል የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓትን ማጎልበት | | | | 1 | | | | | | | | | | | | | ቀልጣፋ የፋይናንስ አገልግሎትን | ፕ.ል.ኮ |

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| 4.1 | የፋይናንስ መመሪያና ደንብን ተከትሎ ክፍያዎችን መፈጸም | በመቶኛ | 100 | 100 | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | | |
| 4.2 | የ2014 የኮሚሽኑን የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በኢፍሚስ በየወቅቱ ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት መላክ | በቁጥር | 12 | 12 | | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | | |
| 5 | የውስጥ ኦዲት ሥራዎችን ማከናወን | | | | 1 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ክ |
| 5.1 | የ2013 በጀት ዓመት የመዝጊያ ቆጠራ ማከናወን | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 5.2 | የ2013 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | | | | | | | | | | አመታዊ የኦዲት ሪፖርት | |
| 5.3 | የ2014 በጀት ዓመት የየሩብ ዓመት የፋይናንስና የንብረት ኦዲት ማድረግ | በቁጥር | 4 | 4 | | | | | 1 | | | 1 | | | 1 | | | የሩብ አመት የኦዲት ሪፖርት | |
| 5.4 | የድንገተኛ ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና የፕሮጀክት ሂሳቦችን እንደአስፈላጊነቱ የኦዲት ምርመራ ማከናወን | በቁጥር | | 1 | | | | | | | | | | | | | | የተደረገ ኦዲትና ኢንስፔክሽን | |
| 5.5 | በኦዲት ግኝቶች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ክትትል ማድረግ | በመቶኛ | | 100 | | | | | 100 | | | 100 | | | 100 | | | | |
| 6 | የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | 1 | | | | | | | | | | | | | | ፕ.ል.ክ |
| 6.1 | የተቋሙ ሰራተኞች በህፃናትና በሴቶች መብት ዙሪያ የግንዛቤ | በቁጥር | | 1 | | | | | | | | | | | 1 | | | | |

| ተ.ቁ | የ2014 በ.ዓ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት | የ2014 እቅድ ግብ | | | | የድርጊት መርሃ-ግብር | | | | | | | | | | | | የግብ ውጤት | ፈፃሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | | | 3ኛ ሩብ ዓመት | | | 4ኛ ሩብዓመት | | | | |
| | | መለኪያ | መነሻ | ኢላማ | ክብደት | ሐ | ነ | መ | ጥ | ሕ | ታ | ጥ | የ | መ | ሚ | ግ | ሰ | | |
| | ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6.2 | የተቋሙን ሴት ሰራተኞች በራስ የመተማመንና የአመራር ብቃትና ክህሎት ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና መስጠት | በቁጥር | | 1 | | | | | | | 1 | | | | | | | | |
